በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ 206661

ህዳር 27 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካቾች ፡ 1ኛ. መንግስቱ ከፋለ } አልቀረቡም

2ኛ. አቶ ሳምሶን ሃይሌ

ተጠሪ ፡ ጃርኮ ኮንሰልቲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር- ጠበቃ ጥበቡ ምህረቴ -ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የስራ ውል መቋረጥን ተከትሎ የቀረበ የአሰሪ እና ሰራተኛ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካቾች ከሳሾች ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

አመልካቾች ግንቦት 29 ቀን 2011 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት ክስ በተጠሪ ድርጅት ውስጥ 1ኛ አመልካች በአስታክትሲሺያን ሙያ 2ኛ አመልካች በሎጅስቲክስ ኦፊሰር የስራ መደብ ስናገለግል ቆይተን ተጠሪ የድርጅቱ ስራ ስለቀዘቀዘ የስራ መደባችሁን ለመሰረዝ ተገደናል በሚል ከስራ አሰናብቶናል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የስራ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ውላችንን ያቋረጠው በህገወጥ መንገድ ስለሆነ ተገቢ ክፍያዎችን እንዲከፍል ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ ሐምሌ 22 ቀን 2011 ዓ.ም. ጽፎ ባቀረበው መልስ አመልካቾች ከስራ የተሰናበቱት የድርጅቱ የስራ እንቅስቃሴ በመቀዝቀዙ እና ትርፍ እያሽቆለቆለ በመምጣቱ አንዳንድ የስራ መደቦችን መሰረዝ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህ ምክንያት የአመልካቾች የስራ መደብ የተሰረዘ ሲሆን ወደሌላ የስራ መደብም አዛውረን ማሰራት ባለመቻላችን የስራ ውላቸውን ለማቋረጥ ተገደናል፡፡ በመሆኑም አመልካቾች በህጉ መሰረት የተሰናበቱ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክርክሩን መርምሮ ማስጠንቀቂያ መስጠቱን፣ የስራ ስንብት እና የአመት እረፍት ክፍያ መከፈሉን ክሱ ሲሰማ ግራ ቀኙ ተማምነዋል፡፡ የተጠሪ ገቢ እና ትርፍ እየቀነሰ መምጣቱን ተጠሪ ካቀረበው የ2009 እና 2010 በጀት አመት ትርፍ መረዳት ተችሏል፡፡ ይህም የስራ መደብን ለመሰረዝ በቂ ምክንያት ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 28/1/መ መሰረት ስንብቱ ህጋዊ ነው፡፡ ነገር ግን በአዋጁ አንቀጽ 40/3 መሰረት አመልካቾች ተጨማሪ የስንብት ክፍያ ሊከፈላቸው ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪ ለአመልካቾች ተጨማሪ የስንብት ክፍያ ሊከፈል ይገባል በመባሉ ቅር በመሰኘት ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 28/1/መ መሰረት የተሰናበተ ሰራተኛ በአዋጁ አንቀጽ 40/3 መሰረት ተጨማሪ የስንብት ክፍያ እንደሚከፈለው አልተደነገገም፡፡ በመሆኑም አመልካቾች ተጨማሪ የስንብት ክፍያ ሊከፈላቸው አይገባም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አሻሽሏል፡፡

አመልካቾች በሚያዝያ 21 ቀን 2013 ዓ.ም. የተጻፈ የሰበር ቅሬታ ያቀረቡት ስንብቱ ህጋዊ ነው እንዲሁም ተጨማሪ የስንብት ክፍያ ሊከፈላቸው አይገባም መባሉን በመቃወም ለማሳረም ነው፡፡ የቅሬታው ይዘት ተጠሪ የስራ ወሉን ያቋረጠበት ምክንያት ትርፍ ቀንሷል በሚል ነው፡፡ ትርፍ ቀንሷል ወይስ አልቀነሰም የሚለው ፍሬ ነገር የተመዘነበት እና ህጉ የተተረጎመበት መንገድ መሰረታዊ ህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ ስንብቱ በስር ፍርድ ቤት ህጋዊ ነው በመባሉ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መስቀለኛ ይግባኝ አቅርበን በዝምታ ታልፎብናል፡፡ የስራው መሰረዝ ምክንያት በአሰሪ እና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 28/3/ለ ላይ የተጠቀሰው ምክንያት በመሆኑ ቅነሳው የሚከናወነው በአዋጁ አንቀጽ 29 መሰረት ነው፡፡ በአንቀጽ 29 መሰረት የተፈጸመ ስንብት ከሆነ ደግሞ በአንቀጽ 40/3 መሰረት ተጨማሪ የስንብት ክፍያ ሊከፈል ይገባል፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ይታረምልን የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት የአመልካቾችን የሰበር ቅሬታ መርምሮ አመልካቾች ክፍያ አይገባቸውም የመባሉን አግባብነት ከአሰሪ እና ሰራተኛ አዋጁ አንቀጽ 24፣28፣29 እና 40/3 አንጻር ለማጣራት ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ ትዝዛዝ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በመስከረም 28 ቀን 2014 ዓ.ም. ጽፎ ባቀረበው መልስ የድርጅቱ ትርፍ ቀንሷል ወይስ አልቀነሰም የሚለው የፍሬ ነገር ክርክር እና በማስረጃ የሚጣራ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ማስረጃን መዝነው ትርፍ መቀነሱን አረጋግጠዋል፡፡ ስለዚህ ስንብቱ ህጋዊ ነው በመባሉ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡ አመልካቾች የማስጠንቀቂያ፣ የስንብት እና የአመት እረፍት ክፍያ የተከፈላቸው መሆኑ አልተካደም፡፡ በመሆኑም ተጨማሪ የስንብት ክፍያ ሊከፈል አይገባም መባሉ ተገቢ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካቾችም የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር ቅሬታቸውን አጠናክረዋል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር የአመልካቾች የስራ ስንብት ህጉን የተከተለ ነው ወይስ አይደለም? እና አመልካቾች ተጨማሪ የስንብት ክፍያ ሊከፈላቸው ይገባል ወይስ አይገባም? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ በስር ፍርድ ቤት ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች እና ከተገቢው ህግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በመጀመሪያም የአመልካቾች ስንብት ህጋዊ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ስንመለከት ለአመልካቾች የስራ ስንብት ምክንያት የሆነው የተጠሪ ትርፍ እየቀነሰ በመሄዱ የአመልካቾች የስራ መደብ ተሰርዟል በሚል ነው፡፡ አመልካቾች በበኩላቸው ተጠሪ የስራ መደባቸውን መሰረዙን ክደው ያልተከራከሩ ከመሆኑም በላይ የስር ፍርድ ቤት በምስክሮች ያረጋገጠው ፍሬ ነገር መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ እንዲሁም አመልካቾች ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው እና የስንብት ክፍያ የተከፈላቸው መሆኑም ተረጋግጧል፡፡ አመልካቾች አጥብቀው የሚከራከሩት የተጠሪ ስራ እየቀዘቀዘ ትርፍም የቀነሰ ሄዷል የሚለው በአግባቡ አልተረጋገጠም በሚል ነው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ ያቀረበው የ2009 እና የ2010 በጀት አመት ትርፍ መጠን የተጠሪ ስራ እየተቀዛቀዘ እና ትርፍ እየቀነሰ መሄዱን ያሳያል፡፡ ይህ ደግሞ የስራ መደብ ለመሰረዝ በቂ ምክንያት ስለሆነ የአመልካቾች ስንብት ህጋዊ ነው የሚል መደምደሚያ ደርሷል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ አመልካቾች ያቀረቡት አንዱ ቅሬታ ስንብቱ ህጋዊ ነው መባሉን በመቃወም ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ባቀረበው የይግባኝ ቅሬታ ላይ መስቀለኛ ይግባኝ አቅርበን በዝምታ ታልፎብናል የሚል ነው፡፡ እኛም የአመልካቾች መስቀለኛ ይግባኝ በይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዝምታ ታልፏል አልታለፈም? የሚለውን ለማጣራት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመዝገብ ቁጥር 250120ን አስቀርበን ተመልክተናል፡፡ መዝገቡን ተመልክተን የተረዳነው አመልካቾች እንዳሉት መስቀለኛ ይግባኝ ማቅረባቸውን፣ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱም የአመልካቾችን መስቀለኛ ይግባኝ መስማቱን እና በጥቅምት 27 ቀን 2013 ዓ.ም. በዋለው ችሎት 2ኛ ተጠሪ በተገኙበት መስቀለኛ ይግባኙን ባለመቀበል ብይን መስጠቱን ነው፡፡ በመሆኑም አመልካቾች መስቀለኛ ይግባኝ አቅርበን በዝምታ ታልፎብናል በማለት ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት የለውም፡፡

እንደሚታወቀው የስራ ውል በህግ ወይም በስምምነት በአሰሪው ወይም በሰራተኛው አነሳሽነት እንደሚቋረጥ በአሰሪ እና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 23 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ላይ ተመልክቷል፡፡ በማስጠንቀቂያ ወይም ያለማስጠንቀቂያ በአሰሪው አነሳሽነት የስራ ውል ሲቋረጥ የአሰሪ እና ሰራተኛ ጉዳይ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አዋጁ ያስቀመጠውን የስራ ውል ማቋረጫ ምክንያት ብቻ መሰረት በማድረግ ከሆነ ስንብቱ ህጋዊ ይሆናል፡፡ በተቃራኒው አሰሪው ሰራተኛውን በማስጠንቀቂያ ወይም ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውልን ለማቋረጥ የሚያስችሉ ምክንያቶች መኖራችን ሳያረጋግጥ የስራ ውል የሚያቋርጥ ከሆነ ስንብቱ ህገወጥ ይሆናል፡፡ ስለዚህ የአመልካቾች ስንብት ህጋዊ ነው ወይስ አይደለም? የሚል መደምደሚያ ላይ ለመድረስ የስንብቱ ምክንያት በአሰሪ እና ሰራተኛ አዋጁ የተመለከተ ስንብት ምክንያት መሆኑን መመርመር ተገቢ ነው፡፡

ከላይ እንደተገለጸው ተጠሪ አመልካቾችን ከስራ ያሰናበተው የስራ መደባቸው ተሰርዟል፤ በሌላ የስራ መደብ ላይም መመደብ አልቻልኩም በማለት ነው፡፡ የስራ መደቡን የሰረዘበት ምክንያት ደግሞ የድርጅቱ ስራ እና ትርፍ እየቀነሰ በመሄዱ መሆኑን ገልጾ ተከራክሯል፡፡ በአሰሪ እና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 28/1/መ ላይ ሰራተኛው የያዘው የስራ መደብ በበቂ ምክንያት ከተሰረዘና ሰራተኛውን ወደሌላ የስራ መደብ ማዛወር ካልተቻለ አሰሪው ማስጠንቀቂያ በመስጠት የስራ ውል ሊያቋርጥ እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ መረዳት የሚቻለው የስራ መደብ መሰረዙ ብቻውን ሰራተኛውን ከስራ ለማሰናበት በቂ ምክንያት አለመሆኑን ነው፡፡ የስራ መደቡ መሰረዝ ሰራተኛን ለማሰናበት በቂ ምክንያት ሊሆን የሚችለው የስራ መደቡ በበቂ ምክንያት መሰረዙ እና አሰሪው ሰራተኛውን በሌላ የስራ መደብ ላይ መድቦ ለማሰራት ጥረት አድርጎ መመደብ ያልቻለ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡ ይህም ማለት አሰሪው በዘፈቀደ ያለበቂ ምክንያት የሰራተኛውን የስራ መደብ በመሰረዝ እና በሌላ የስራ መደብ ላይ ለመመደብ ጥረት ሳያደርግ ሰራተኛውን ማሰናበት አይችልም ማለት ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የስር ፍርድ ቤቶች የተጠሪ ስራ እየቀዘቀዘ ትርፍም እየቀነሰ መሄዱን በማስረጃ ያረጋገጡት ፍሬ ነገር ነው፡፡ እንደሚታወቀው ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ድ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ መሰረት የተሰጠው ስልጣን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸውን ውሳኔዎች ማረም ነው፡፡ ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ማስረጃን መዝነው የደረሱበትን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ይህ ችሎት እንዲመለከት ስልጣን አልተሰጠውም፡፡ በመሆኑም የተጠሪ ስራ ተቀዛቅዟል ወይስ አልተቀዛቀዘም እንዲሁም ትረፋ ቀንሷል ወይስ አልቀነሰም የሚለው በማስረጃ የሚጣራ የፍሬ ነገር ክርክር በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ማስረጃን መዝነው የተጠሪ ትርፍ ቀንሷል በሚል የደረሰበት መደምደሚያ ይህ ችሎት እንዳለ የሚቀበለው ነው፡፡

በመቀጠል የተጠሪ ትርፍ መቀነሱ እንዲሁም ስራው መቀዝቀዙ በማስረጃ ከተረጋገጠ የስራ መደብን ለመሰረዝ በቂ ምክንያት ይሆናል ወይ? የሚለውን ስንመለከት ይህ ምክንያት ሰራተኛን ለመቀነስ በቂ ምክንያት መሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 28/3/ለ ላይ ተመልክቷል፡፡ ነገር ግን የስራ መደብን ለመሰረዝ በቂ ምክንያት ስለመሆኑ በግልጽ አልተመለከተም፡፡ ከስራ መደብ መሰረዝ ጋር በተያያዘ በአዋጁ አንቀጽ 28/1/መ ላይ በቂ ምክንያት ያስፈልጋል በሚል የተገለጸ በመሆኑ በቂ ምክንያት ምንድነው የሚለውን መመዘን ለፍርድቤቶች የተሰጠ ስልጣን ነው፡፡ በአንድ የስራ መደብ ላይ አንድ ሰራተኛ ብቻ የሚሰራ ከሆነ እና አሰሪው ትርፉ እየቀነሰ ስራው እየቀሰቀዘ ሲሄድ ድርጅቱን ውጤታማ ለማድረግ በአንድ ሰራተኛ የተያዘን የስራ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

መደብ ቢሰርዝ የሰረዘበት ምክንያት በቂ ምክንያት ነው ተብሎ ሊወሰድ የሚችል ይሆናል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ስራው እየቀዘቀዘ መሄዱን እና ትርፉ መቀነሱን በማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ ይህ ምክንያትም የስራ መደብን ለመሰረዝ በቂ ምክንያት ነው፡፡ እንዲሁም ተጠሪ አመልካቾችን በሌላ የስራ መደብ መድቦ ለማሰራት የማይችል መሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች ስለተረጋገጠ ስንብቱ በአዋጁ አንቀጽ 28/1/መ መሰረት ህጋዊ ነው በመባሉ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስንብቱ ህጋዊ ነው ከተባለ ለአመልካቾች ተጨማሪ የስንብት ክፍያ ሊከፈል ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለውን ነጥብ ስንመለከት በአሰሪ እና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጁ አንቀጽ 40/3 ላይ የስራ ውል በአዋጁ አንቀጽ 24/4 እና በአንቀጽ 29 መሰረት ሲቋረጥ ተጨማሪ የስንብት ክፍያ ሊከፈል እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡ ይህም ማለት በመክሰር ወይም በሌላ ምክንያት ድርጅቱ ለዘለቄታው ሲዘጋ እና ህጉ ባስቀመጠው ምክንያት የሰራተኛ ቅነሳ ሲደረግ ተጨማሪ የስንብት ክፍያ ይፈጸማል፡፡ ከነዚህ ምክንያቶች ውጪ የስራ ውል ሲቋረጥ ግን ተጨማሪ የስንብት ክፍያ እንደሚከፈል በአዋጁ አንቀጽ 40/3 ላይ አልተመለከተም፡፡ ስለዚህ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካቾች የስራ ስንብት በአዋጁ አንቀጽ 28/1/መ መሰረት ህጋዊ ነው ካለ በኋላ ተጠሪ ተጨማሪ የስንብት ክፍያ እንዲከፍል መወሰኑ የአዋጁን አንቀጽ 40/3 ድንጋጌ የሚቃረን መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንን ስህተት ማረሙ ተገቢ ነው ከሚባል በስተቀር በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ባለመኖሩ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1ኛ. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 250120 በጥቅምት 28 ቀን 2013 ዓ.ም. ሰጠው ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 348/1 መሰረት ጸንቷል፡፡

2ኛ. በዚህ ፍርድ ቤት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

## ትእዛዝ

የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 250120 በመጣበት አኳኋን ተመላሽ ይደረግ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም